# ኢትዮጵያ፤ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሪፖርት (2013)

ኢትዮጵያ ለግዳጅ ሥራ እና ለወሲብ ንግድ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የተዳረጉ ወንዶች፣ ሴቶች እና ሕፃናት መነሻ፤ በተወሰነ ደረጃም መዳረሻ አገር ናት፡፡ ከኢትዮጵያ የገጠር አካባቢዎች የሚወጡ ወጣት ሴቶች፤ በአገሪቱ ውስጥ በቤት ሠራተኝነት እና፣ አልፎ አልፎም፣ በሴተኛ አዳሪነት ይበዘበዛሉ፤ ወጣት ወንዶች ደግሞ በባህላዊ ሽመና፣ በእረኝነት፣ እና በጎዳና ላይ ንግድ በግዳጅ እንዲሰሩ ይደረጋሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን ልጃገረዶች ከኢትዮጵያ ውጪም በተለይ ጂቡቲ እና ደቡብ ሱዳን ውስጥ በቤት ሠራተኝነት እና በሴተኛ አዳሪነት እንዲሰሩ ይገደዳሉ፤ ኢትዮጵያውያን ወጣት ወንዶች ደግሞ ጂቡቲ ውስጥ በሱቅ ሰራተኝነት፣ በተላላኪነት፣ በቤት ሰራተኝነት፣ በስርቆት እና በጎዳና ላይ ልመና ለግዳጅ ሥራ ይዳረጋሉ፡፡

ከመሰረታዊ ትምህርት ያልዘለለ ዕውቀት ያላቸው በርካታ ወጣት ሴቶች በመካከለኛ ምሥራቅ አገሮች፣ በሱዳን እና ደቡብ ሱዳን ለቤት ሠራተኝነት ይዳረጋሉ፡፡ ሥራ ፍለጋ ሲሰደዱም አብዛኞቹ ጂቡቲ፣ ግብጽ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን ወይም የመንን እንደመሸጋገሪያ ይጠቀማሉ፡፡ አንዳንድ ሴቶች ሊሄዱ ካሰቡበት አገር ለመድረስ እንደመሸጋገሪያነት ያረፉበት አገር ታግተው ለብዝበዛ ይዳረጋሉ፡፡ በመካከለኛው ምሥራቅ አገራት በቤት ሰራተኝነት የተሰማሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት፣ ደሞዝ ክልከላ፣ እንቅልፍ መነፈግ፣ የፓስፖርት መያዝ፣ በቤት ውስጥ መታገት እና ግድያን ጨምሮ አስከፊ ጥቃቶች ይደርሱባቸዋል፡፡ የሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኢትዮጵያውንን ወደ ውጭ አገራት ለስራ የሚልኩ ድርጅቶች እ.ኤ.አ. በ2012 ከ198,000 የስራ ፈላጊዎች ማመልከቻ መቀበላቸውን፤ ይህም ቁጥር በ2011 ካመለከቱት ጋር ሲነጻጸር ከእጥፍ በላይ መጨመሩን ቢያስታውቅም፣ ይህ ቁጥር ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ከሚሰደዱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከ30 እስከ 40 በመቶ ብቻ የሚወክል ሊሆን እንደሚችል ገምቷል፡፡ ከ60 እስከ 70 በመቶ የሚሆኑት ሠራተኞች በሕገ ወጥ ደላሎች አማካኝነት ለህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወይንም ስደት ይዳረጋሉ፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ኢትዮጵያውያን ሴቶች ለመቀጠር በማሰብ ከአገር ከወጡ በኋላ፣ በወሲብ ንግድ ቤቶች፣ በማዕድን ማውጫ ቦታዎች፣ ሱዳን እና ደቡብ ሱዳን ውስጥ በሚገኙ ነዳጅ ዘይት ማውጫ አካባቢዎች ለወሲብ ንግድ ብዝበዛ ይዳረጋሉ፤ ይኸው ሁኔታ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ጥቃት ከሚያደርሱባቸው አሠሪዎቻቸው ጠፍተው ካመለጡ በኋላም ያጋጥማቸዋል፡፡ የዳበረ የሙያ ክህሎት ሳይኖራቸው ወደ ሳዑዲ አረቢያ፣ የባህረ-ሰላጤው አገሮች እና ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ከሚሰደዱ ኢትዮጵያውያን ወንዶች አንዳንዶቹ በእነዚህ አገራት ለግዳጅ የጉልበት ሥራ ይዳረጋሉ፡፡ እ.ኤ.አ በ2012 ለወሲብ እና ለጉልበት ብዝበዛ የታለመ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ የሆኑ ዘጠኝ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ፣ ሰባት ደግሞ በእንግሊዝ መኖራቸው ታውቋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ የስደተኛ ካምፖች ውስጥ ከሚኖሩ ኤርትራውያን መካከል አንዳንዶቹ በፈቃደኝነት ከካምፑ ሲወጡ፤ ሌሎቹ ደግሞ ከካምፑ ተጠልፈው ከተወሰዱ በኋላ በግብጽ የሲናይ በረሃ ለሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተዳርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ ለሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች መሸጋገሪያ ከመሆንም በተጨማሪ መዳረሻ አገር ናት፡፡ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የሩዋንዳ ዜጎች ከኪጋሊ ተጓጉዘው አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ በግዳጅ ስራ እና በሴተኛ አዳሪነት ተበዝብዘዋል፡፡ ከነዚህም አንዳንዶቹ ወደ አውሮፓ አገራት ተወስደው በሴተኛ አዳሪነት እንዲሰማሩ ተገደዋል፡፡ በሌላ በኩል የታንዛኒያ ፍርድ ቤት ስድስት የታንዛኒያ ዜጎችን ለግዳጅ

የጉልበት ብዝበዛ ወደ ኢትዮጵያ በመላክ በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል በተከሰሱ ሶስት ሰዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ አሳልፏል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን ስለማስወገድ የተቀመጡትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ባያሟላም፣ ከፍተኛ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፡፡ መንግሥት ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን የሚመለከተውንና እ.ኤ.አ. በ2000 የተፈረመውን የተባበሩት መንግስታት ፕሮቶኮል ያጸደቀ ሲሆን፣ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የፈጸሙ ወንጀለኞች ሕግ ፊት ቀርበው እንዲቀጡ አድርጓል፡፡ ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ መንግሥት በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እና ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር በማሻገር መካከል ያለውን ልዩነት ያለመረዳት ችግር በመኖሩ፣ ወንጀሉን ለማስቆም ለሚደረጉ ጥረቶች እንቅፋት ሆኗል፡፡ መንግስት የሕገወጥ ዝውውር ሰለባ የሆኑ ሰዎችን ጨምሮ በችግር ውስጥ ለሚገኙ ስደተኞች የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎቶች እና የሎጂስቲክ ድጋፍ የሚያደርግ ማዕከል በአፋር ክልል አቋቁሟል፡፡ የክልል መስተዳድሮችም ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ስልጠናዎችን የሰጡ ሲሆን፤ የሕገወጥ ዝውውርን ለማስቆም በሚደረጉ ጥረቶችን ዙሪያ የሚያስተባብሩ ግብረ ኃይሎችን አቋቁመዋል፡፡ መንግሥት በአገር ውስጥ የሚካሄዱ ሕገወጥ የሰዎች ማዘዋወር ወንጀሎችን መመርመሩንና በአገሪቱ ሕግ መሰረት ለፍርድ ማቅረቡን ቢገልጽም፣ በዚህ ረገድ የተደረጉ ጥረቶችን የሚያመላክቱ መረጃዎች ለማጠናቀር አለመቻሉ አሳሳቢ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች የሚያደርገው ድጋፍም አገልግሎቱን ከሚሰጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በሙሉ ፍላጎት እና ወጥነት ባለው መልኩ በትብብር ለመስራት ባለመቻሉ ሳቢያ ስኬታማ ሊሆን አልቻለም፡፡ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚገኙ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች የሚሰጡት ውሱን እና ወጥነት የሌለው ድጋፍ ከችግሩ ስፋት ጋር ሲነፃፀር በቂ አልነበረም፤ በእነዚህ ኤምባሲዎች ውስጥ የሠራተኞች ጉዳይ አታሼ እንዲመደብ የሚፈቅድ ሕግ ቢኖርም፤ የአገሪቱ ፓርላማ ለዚህ የሚሆን በጀት አልመደበም፡፡




**በኢትዮጵያ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለማስቆም የሚረዱ የመፍትሄ ሐሳቦች** ፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ለተዘረዘሩ ለወሲብ ንግድና ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎች የተቀመጡትን ቅጣቶች ማክበድ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንቀጽ 597 እና 635ን ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ግልፅ ትርጉም ባካተተና ወንድ የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች ራሱን በቻለ አንቀጽ በሕጉ እንዲሸፈኑ በሚያደርግ መልኩ ማሻሻል፣ እንዲሁም ቅጣቶችን በሌሎች ከባድ ወንጀሎች ላይ ከሚጣሉ ቅጣቶች ጋር እንዲጣጣሙ በሚያደርግ መልኩ ማሻሻል፤ የፖሊስን፣ የወንጀል ምርመራ አቅም እና በመላ አገሪቱ ያሉ የዳኝነት አካላት በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማሳደግ፣ በአገር ውስጥ የሚፈፀመውን ህገወጥ የሕጻናት ዝውውር ወንጀል ፈጻሚዎችን ሕግ ፊት ለማቅረብ እንዲቻል ይረዳል፡፡ በጉልበት ብዝበዛ እና በወሲብ

ንግድ ዓላማ የሚካሄዱ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎችን በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንቀጽ 596፣ 597 እና አንቀጽ 635 መሰረት ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ውስጥ የሠራተኞች ጉዳይ አታሼዎች ለመመደብ እንዲቻል አስፈላጊውን በጀት መያዝ፤ በውጭ አገር ለሚሾሙ ዲፕሎማቶች እና የሥራ ቅጥር ውሎችን ሕጋዊነት ለሚያረጋግጡ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ የሥራ ኃላፊዎች ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መደበኛ ሥልጠናዎች የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እና ሌሎች አገራት ለሚጓዙ ስደተኛ ሠራተኞች በሚሰጠው የቅድመ ጉዞ ስልጠና ውስጥ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና የሰራተኛ መብትን የሚመለከት መረጃ ማካተት፤የመካከለኛው ምስራቅ አገራት መንግስታት ለኢትዮጵያውያን ሰራተኞች የሚያደርጉትን ጥበቃ እንዲያሻሽሉ ጥረት ማድረግ፤ በመንግሥትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚተዳደሩ የሰለባዎች መጠለያዎች ያልተቋረጠ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በጀት መመደብን ጨምሮ ከውጭ ለሚመለሱ የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ደረጃ ለማሳደግ ከአገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ መሥራት፤ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለማስቆም የተቋቋመውን ብሔራዊ ግብረ ኃይል ውጤታማነት ማሻሻል፣ እንዲሁም በክልል ደረጃ በአገር ውስጥ ስለሚፈፀሙ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎች ግንዛቤ ማሳደግን ዓላማ ያደረገ ዘመቻ ማካሄድ፡፡

## በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ፈጻሚዎች ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች

ሪፖርቱ በሚሸፍነው ወቅት ውስጥ የኢትዮጵያ መንግስት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመቆጣጠር ያወጣውን ሕግ በስራ ላይ ለማዋል ጥረት ማድረጉን እንደቀጠለ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀፅ 596 (ለባርነት መዳረግ)፣አንቀፅ 597 (ሕገወጥ የሴቶች እና የሕጻናት ዝውውር) እንዲሁም አንቀጽ 635 (የሴቶች እና የሕፃናት ዝውውር) ለወሲብ ንግድ ዓላማ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መፈጸም የተከለከለ ተግባር እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ለወሲብ ንግድ የሰዎች ዝውውር መፈጸምን የሚከለክለው አንቀጽ 635 ከአምስት ዓመት ያልበለጠ የእሥር ቅጣት ይጥላል፤ይህ በራሱ ከባድ ሊባል የሚችል ቢሆንም፣ አስገድዶ መድፈርን ለመሳሰሉ ሌሎች ከባድ ወንጀሎች ከተቀመጡ ቅጣቶች ጋር ሲነፃፀር ግን አነስተኛ ነው፡፡ አንቀጽ 596 እና 597 ባርያ አሳዳሪነት እና የጉልበት ብዝበዛ ዓላማ ያለው የሰዎች ዝውውር ሕገወጥ ተግባራት እንደሆኑ የሚደነግጉ ሲሆን፤ ለነዚህም ከአምስት እስከ ሃያ ዓመታት የሚደርስ እና ከባድ የእስር ቅጣት ይጥላሉ፡፡ ነገር ግን አንቀጽ 597 እና 635 ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የጠራ ትርጉም ካለመስጠታቸውም ሌላ፤ በአዋቂ ወንዶች ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ቅጣትን አያካትትም፡፡ በመሆኑም ከሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ጋር የሚያያዙ ጥፋቶችን ተከትሎ ክስ ለመመስረት እምብዛም ጥቅም ላይ አይውሉም፡፡ ከዚህ ይልቅ፣ በጉልበት ብዝበዛ ዓላማ የሚፈፀሙ ድንበር ዘለል የሰዎች ዝውውርን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለመዳኘት አዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉት አንቀጽ 598 (ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ወደ ውጭ አገር ስለ መላክ) እና አንቀፅ 571 (የሌላ ሰውን ሕይወት አደጋ ላይ መጣል) ናቸው፡፡ የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሕጋዊ ትርጓሜ አለመኖር ፌደራል ፖሊስ እና ፍትሕ ሚኒስቴር እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን የመመርመር እና ለፍርድ የማቅረብ አቅም ገድቦታል፡፡ ፌደራል ፖሊስ የሰዎች ዝውውር ወንጀልን በመመርመር፣ እንዲሁም ቀደም ካሉ ዓመታት ቁጥራቸው ከፍ ያለ ክሶችን ለፍርድ በማቅረብ እና እልባት እንዲያገኙ በማድረግ ከፌደራል አቃቤ ሕግ ጋር በመተባበር ረገድ መሻሻል ማሳየቱን ቀጥሏል፡፡ የተደራጀ ወንጀል ምርመራ ዩኒት ውስጥ ያለው የፌደራል ፖሊስ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እና የአደንዛዥ ዕጽ

ዝውውር መቆጣጠሪያ ክፍል ሪፖርቱ በሚሸፍነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በ133 መዝገቦች በታዩ 166 ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ፈጻሚዎች ላይ ምርመራ አድርጓል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ ስምንት ግለሰቦች በምርመራ ላይ ነበሩ፡፡ በቀሪዎቹ 158 ግለሰቦች ላይ በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባቸው የነበረ ሲሆን፤ ከነዚህም 58 ክሶች በመታየት ላይ ናቸው፡፡ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 11ኛ ወንጀል ችሎት በ100 ክሶች ላይ የጥፋተኝነት ብይን ሰጥቶ (እ.ኤ.አ. በ2011 ጥፋተኝነት የተበየነባቸው 77 ነበሩ) ከሁለት ዓመት እስከ 16 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ፈርዶባቸዋል፡፡ መንግስት በአገር ውስጥ የሚፈጸሙ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎችን በመመርመር እና ክስ በመመስረት ረገድ ያደረገውን ጥረት የሚያሳይ መረጃ አልሰጠም፡፡ በመላ አገሪቱ የሚገኙ የክልል ሕግ ማስከበር አካላት በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እና ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር በማሻገር መካከል ያለውን ልዩነት ያለመረዳት ችግር የሚታይባቸው ሲሆን፤ ጉዳዮችን በአግባቡ የመመርመር ብሎም ተያያዥ መረጃዎችን የመሰብሰብ እና የማደራጀት አቅም ውሱንነትም አለባቸው፡፡ በዓመቱ ውስጥ መንግሥት ለሕግ አስከባሪዎች በተለይ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ያተኮረ ሥልጠና ባይሰጥም፤ የፖሊስ አባላት እና ሌሎች ኃላፊዎች በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተሰጡ ስልጠናዎችን ተከታትለዋል፡፡ መንግሥት ከሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ፈፃሚዎች ጋር ተባብረዋል በተባሉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ላይ ምርመራ ማደረጉን፣ ክስ መመስረቱንም ሆነ ማስቀጣቱን በሚመለከት ምንም ሪፖርት አላቀረበም፡፡

## ለህገወጥ ዝውውር ሰለባዎች የተደረገ ጥበቃ

በሪፖርት ዓመቱ መንግሥት ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች ያደረገው ድጋፍ ውሱን ነበር፡፡ በዚህ ረገድ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ለህገወጥ ዝውውር ሰለባዎች የሚያስፈልገውን የጥበቃ ኃላፊነት ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ሰጥቷል፡፡ ለሌሎች ወንጀሎች ሰለባዎች የሚያደርገውን እንክብካቤ በተለይ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች ማድረግ አልቻለም፡፡ እ.ኤ.አ. በሐምሌ ወር 2012 ፌዴራል ፖሊስ እና ዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (IOM) በአፋር ክልል የአስቸኳይ ዕርዳታ ማዕከል አቋቁመዋል፡፡ በማዕከሉ ፖሊስ እና የአካባቢው የጤና ባለሙያዎች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎችን ጨምሮ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ስደተኞች ሕይወት አድን ሕክምና፣ አልሚ ምግብ፣ ጊዜያዊ መጠለያ፣ወደ መኖሪያ ቀዬአቸው የሚያደርስ መጓጓዣ እንዲሁም የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ በአጠቃላይ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች የተደረጉ የጤና እንክብካቤ እና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች እንደ ሌሎች ወንጀሎች ሰለባዎች ሁሉ በመንግስት ሆስፒታሎች ተሰጥተዋል፡፡ መንግሥት ለአብዛኞዎቹ የሕገወጥ ዝውውር ሰለባዎች ድጋፍ ማድረግን በሚመለከት በከፍተኛ ደረጃ ኃላፊነቱን መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ቢሰጥም፣ ለነዚህም ድርጅቶች ምንም ዓይነት የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ ድጋፍ አያደርግም፡፡ በመሆኑም የህገወጥ ዝውውር ሰለባዎች አስተማማኝ እንክብካቤ አያገኙም፡፡ አብዛኞዎቹ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ሥር ያሉ የድጋፍ ተቋማት ፕሮጀክትን መሠረት ባደረገ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ጥገኛ በመሆናቸው በዘላቂነት አገልግሎት ሊሰጡ አይችሉም፡፡ እ.ኤ.አ. በ2012 ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች ታስረው የቆዩበት፣ ለወህኒ የተዳረጉበት ወይንም መከሰሳቸውን የሚያመለክት ሪፖርት አልቀረበም፡፡

በውጭ አገር ተቀጥረው ለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን የሚሰጠው የቆንስላ አገልግሎት ውሱን በመሆኑ፣ መንግሥት በዚህ መስክ የሚያደርገው ጥረት ደካማ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ 300 የሚሆኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የሰራተኛ ቅጥር ኤጀንሲዎችን አሰራር የሚቆጣጠረው የሠራተኞች

ቅጥር ልውውጥ አገልግሎቶች አዋጅ ቁጥር 632/2009፤ፈቃድ ያላቸው የአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የሥራ ውል በሚፈርስበት ጊዜ ለሠራተኞች ድጋፍ መስጠት እንዲቻል የተወሰነ ገንዘብ በዝግ ሒሳብ እንዲያስቀምጡ ቢያዝም፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰለባዎችን ወደ ኢትዮጵያ ሲያጓጉዝ ለሚያወጣው የትራንስፖርት ወጪ ከዚህ በዝግ ሒሳብ ከተቀመጠ ገንዘብ አንድም ጊዜ አልተጠቀመም፡፡ በተጨማሪም አዋጁ በውጭ በሚገኙ ኤምባሲዎች ውስጥ የሠራተኞች ጉዳይ አታሼ እንዲቋቋም ቢጠይቅም፣ ፓርላማው በኤምባሲዎች የሰራተኛ ጉዳይ አታሼ ለመመደብ ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በጀት አልያዘም ወይም አዋጁ በስራ ላይ የሚውልበትን እቅድ ወይም የጊዜ ሰሌዳ አላስቀመጠም፡፡ ሪፖርቱ በተዘጋጀበት ወቅት በአዲስ አበባ የቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ባለሥልጣናት እና የኢሚግሬሽን ኃላፊዎች 145 ሴት የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎችን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ወደ አንድ አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ልከዋል፤ ነገር ግን ይህንን ያደረጉት የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ መሆናቸውን ራሳቸው ለተናገሩ ሴቶች ብቻ ነበር፡፡

## ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል የተደረገ እንቅስቃሴ

በሪፖርት ዓመቱ መንግሥት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል የሚያደርገውን ጥረት ቀጥሏል፡፡ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት በተቋቋመው ቴክኒካዊ የምክክር ቡድን አባል የሆኑ ከፌደራል የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እና ኤጀንሲዎች የተወከሉ የሥራ ኃላፊዎች ሳምንታዊ ስብሰባዎችን ያደረጉ ቢሆንም፤ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ፈጻሚዎች የሚዘወተሩ ዘዴዎችን እና ታክቲኮችን በማወቅ፣ እንዲሁም ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በብዛት የሚካሄድባቸውን መነሻ ክልሎች በመለየት በኩል እምብዛም ስኬታማ አልነበሩም፡፡ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ የሚንቀሳቀሰው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ግብረ ኃይል በየሩብ ዓመቱ የሚሰበሰብ ቢሆንም፤ተጨባጭ ውጤቶችን ማምጣት አልቻለም፡፡ በግብረኃይሉ የተዘጋጀው ረቂቅ አገር አቀፍ የፀረ-ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የድርጊት መርኃ ግብር በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ ሲጠበቅ ሶስት ዓመት ሆኖታል፡፡ ሆኖም መንግሥት አስከፊ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስወገድ የተዘጋጀውን አገር አቀፍ የድርጊት መርኃ ግብር እ.ኤ.አ. በታሕሳስ 2012 ያጸደቀ ሲሆን፤ ይህም የሕጻናትን ሕገወጥ ዝውውር የሚከለክሉ አንቀጾች የተካተቱበት ነው፡፡ በሰኔ ወር 2012 በወጣው ሕግ መሰረት፤ መንግስት በመላ አገሪቱ የልደት ምዝገባ እንዲከናወን ቢጠይቅም፤ አንድ ወጥ የሆነ ብሔራዊ መታወቂያ አለመኖሩ ለሕጉ አፈጻጸም እንቅፋት ሆኗል፡፡ ከዚህ ሌላ የመንግሥት ሰነዶች በከፍተኛ ደረጃ ለማጭበርበር ወንጀል የተጋለጡ ናቸው፡፡

እ.ኤ.አ. በሐምሌ 2012 የትግራይ ክልላዊ መንግሥት የወጣቶች እና ስፖርት ጉዳዮች ቢሮ ከዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ጋር በመተባበር ለሕግ አስከባሪ አካላት፣ዓቃብያነ ሕግ፣ ዳኞች እና ሌሎች የመንግሥት ኃላፊዎች መደበኛ ባልሆነ ስደት እና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ሁለት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናሮችን አዘጋጅቶ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ. በሚያዚያ ወር 2012 የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ከዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት (ILO)ጋር በመተባበር ለሕግ አስከባሪ አካላት እና የመንግስት ኃላፊዎች ክልሉ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እየሰጠ ባለው ምላሽ ላይ የተወያየ አውደጥናት አዘጋጅቶ ነበር፡፡ የጋሞ ጎፋ ዞን ኃላፊዎችም ፍርድ ቤት፣ ፖሊስ፣ የዞን ምክር ቤት፣ የሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች እና ፍትህ ቢሮ የተወከሉበት እና በየሩብ ዓመቱ እየተሰበሰበ የሕገወጥ ዝውውር ጉዳዮችን የሚያስተባብር ግብረኃይል አቋቁመዋል፡፡ በተመሳሳይም በዞኑ ስር በሚገኙ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ግብረኃይሎች የተዋቀሩ ሲሆን ከዞኑ ግብረኃይል ይልቅ በየአጭር ጊዜ ስብሰባ ያደርጋሉ፡፡ የደቡብ ብሔሮች፣

ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ እ.ኤ.አ. በ2009 ያወጣውንና አስጎብኚ ድርጅቶችም ሆኑ ቱሪስቶች በወሲብ ቱሪዝም ላይ እንዳይሳተፉ ወይም ሁኔታዎችን እንዳያመቻቹ የሚከለክለውን የቱሪዝም የስነ-ምግባር ደንብ ለመተግበር ወይም ለማስከበር እርምጃ አልወሰደም፡፡

በሪፖርት ዓመቱ መንግሥት ከዮርዳኖስ፣ ኩዌት፣ ኳታር እና ሳዑዲ ዓረቢያ መንግሥታት ጋር የሰራተኞች ስደት ስምምነቶች የተፈራረመ ሲሆን፤ ከተባበሩት ዓረብ ኤሚሬትስ ጋር የሚደረገው ስምምነት በድርድር ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም እነዚህ ስምምነቶች የሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ስለመግታት ማካተታቸውን በየትኛውም ወገን አልተገለጸም፡፡ ኢትዮጵያ በወር 45,000 ሴቶችን በቤት ሰራተኝነት ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ ለመላክ መስማማቷ፤ ኢንዶኔዥያ እና ፊሊፒንስ ዜጎቻችን ላይ ጥቃት ተፈጽሟል በሚል ከአገሪቱ በማስወጣታቸው ምክንያት የተፈጠረውን የሰራተኛ እጥረት ለመሙላት ያግዛል፡፡ በዚህ ስምምነት ምክንያትና በሳዑዲ ዓረቢያ እጨመረ የመጣውን ርካሽ የሰው ጉልበት ፍላጎት የህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ያባብሳል የሚል ግምት አለ፡፡ በኢትዮጵያውያን ስደተኛ ሰራተኞች ላይ ጥቃት ስለመፈጸሙ በመረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም፤ መንግሥት ለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ደኅንነት የሚደረገውን ጥበቃ በማሻሻል ረገድ ከመዳረሻ አገራት መንግሥታት ጋር ለመነጋገር ያሳየው ተነሳሽነት ውስን ነበር፡፡

እ.ኤ.አ. በ2012 የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር 198,000 የውጭ አገር ቅጥር ውሎችን አጽድቋል፤ ከነዚህም አብዛኞቹ ለቤት ሰራተኝነት የሚሰደዱ ሴቶች ናቸው፡፡ ትምሕርት ሚኒስቴር ለስደተኛ ሰራተኞች የስድስት ሣምንታት የቅድመ ጉዞ ስልጠና መስጠት የጀመረ ቢሆንም፤ ስልጠናው ከስራ ጋር የተያያዙ ክህሎቶችና ቋንቋ ላይ በማተኮሩ የሰብዓዊም ሆነ የሰራተኛ መብቶች ጉዳዮች አልተካተቱበትም፡፡ በሪፖርት ዓመቱ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የቁጥጥር ክፍል ሰራተኞች ብዛት ከ130 ወደ 380 ያደገ ሲሆን፤ ይህም የስራ ቦታዎችን በመገምገም እና የመብት ጥሰቶችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በማድረግ በኩል የነበረውን አቅም ያጎለብታል፡፡ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቆጣጣሪዎች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት የሚያስችል ስልጠና አልወሰዱም፤ ምክንያቱም ጉዳዩ ከተሰጣቸው ስልጣን ውጪ እንደሆነ ስለሚታሰብ ነው፡፡ በደሴ ከተማ ላልሰጡት አገልግሎት ክፍያ የተቀበሉ ስድስት የውጭ አገር ሰራተኛ ቅጥር ኤጀንሲዎች በሕግ ማስከበር አካላት ተዘግተዋል፡፡ ይህም ሆኖ በኢትዮጵያውያን የውጭ አገር ሰራተኛ ቅጥር ኤጀንሲዎች ላይ ስልታዊ የሆነ ምርመራ እንዳልተደረገ እና የሕግ ማስከበር አካላትም ኤጀንሲዎቹ በድብቅ የሚሰሯቸውን ሕገወጥ ድርጊቶች ለመከታተል አስቸጋሪ እንደሆነባቸው የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሪፖርት ያስረዳል፡፡ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2000 የወጣውን የተባበሩት መንግሥታት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ፕሮቶኮል እ.ኤ.አ. በሰኔ 2012 አጽድቃለች፡፡

* * * *